# የመጀመሪያው ቀን

ዐየችው
ተያዩ
ዐየና ወደዳት
ቀኑ ማታ ነበር
ወደ ሆቴል ሔዱ
ሁለት ራት መጣ
ብርጭቆ ተጋጨ
ዐየችው
ተያዩ
ዐያት
ተሣሣቁ
በጠረጴዛው ስር
ጭኗ ጭኑን ነካው
ሲያያት
ፈገግ አለች
ዐየችው
ፈገገ
እጇን በጁ ያዘው
ጠበቅ አደረጋት
ጠበቅ አረገችው
ከፈሉና ወጡ
በከሰለው ሌሊት
ሁለቱ ነደዱ
ትንፋሻቸው ጋለ
ቤቱ ተቃጠለ
ፍራሹ ነደደ
ፍቅር ተያያዘ

ገብረ ክረስቶስ ደስታ